Amharic | አማርኛ

# የሰማይ-ጠቀስ ህንጻዎች አዲስ መረጃ

## ጁላይ 2024



ሆምስ ቪክቶሪያ ይህ መኖሪያ ቤት እየተገነባ ያለበትን መሬት የባህላዊ ጠባቂዎች እውቅና ይሰጣል። ላለፉት፣ ለአሁኑ እና ለታዳጊ ሽማግሌዎቻቸው ክብር እንሰጣለን።

# ሮዝ፣ እንኳን ወደ ቤትሽ በደህና መጣሽ!

**ሮዝ እና ቤተሰቧ ወደ ፍሌሚንግተን በመመለሳቸው ደስተኞች ናቸው።**

359 ዘመናዊ፣ ተደራሽ እና ኃይል ቆጣቢ ማህበራዊ እና ተመጣጣኝ ቤቶችን ለመገንባት አከባቢውን ወይም ቦታውን መልሶ የማልማት አካል ሆኖ በቪክቶሪያ ስትሪት ላይ ከቆዩ ቤቶች ከወጡ በርካታ ተከራዮች አንዷ ሮዝ ነበረች።

ሮዝ እና ቤተሰቧ በፍሌሚንግተን ማህበረሰብ ውስጥ መኖር በመጀመራቸው ተደስተዋል።

በዚህ ገጽ ግርጌ ላይ ያለውን የQR ኮድ በመቃኘት ስለ ሮዝ ታሪክ የበለጠ ይወቁ።




> “በመመለሴ ደስተኛ ነኝ። ይህ የኔ ቤት ነው፣ ፍሌሚንግተን የሚመስል ምንም ሰፈር የለም።

www.homes.vic.gov.au/roses-story

# ብዙ እና የተሻሉ ቤቶችን መገንባት

**በካርልተን የሚገኙትን የቀይ ጡብ ረጃጅም ህንጻዎች ጡረታ የማውጣት እና የማደስ ስራ መስራቱን እየቀጠልን ነው።**

ለአዳዲስ ሕንፃዎች፣ የማህበረሰብ ቦታዎች እና አዲስ ቤቶች የሚሆኑ ዕቅዶችን ለመቅረጽ እንዲረዳ ተከራዮችን፣ ባለድርሻ አካላትን እና የካርልተን አካባቢ ማህበረሰብን እያሳተፍን ነው። 196 አሮጌ ቤቶችን በ231 አዲስ ዘመናዊ እና ኃይል ቆጣቢ ማህበራዊ መኖሪያ ቤቶችን ለመተካት ጓጉተናል።



የካርልተን አሮጌ የቀይ ጡብ ረጃጅም ሕንጻዎች ለብዙ እና ለተሻሉ ቤቶች መንገድ ይለቃሉ።

# በሜልበርን ዙሪያ አዲሱ ማህበራዊ መኖሪያ ቤት ይመልከቱ



ቪክቶሪያ ስትሪት (Victoria Street)፣ ፍሌሚንግተን



Oakover Road, Preston



Bangs Street, Prahran

የረጃጅም ሕንጻዎች ዝማኔዎችን ለመከታተል እንዲያግዝዎ ይህንን ያስቀምጡት።

# የመልሶ ማልማት ሂደት እንዴት እንደሚሰራ

1



## ከተከራዮች ጋር መነጋገር እና ተከራዮችን ማዳመጥ

በጠቅላላው ፕሮጀክት ሂደት፣ ብዙ ቦታዎችን ለማደስ ሲታቀድ፣ ተከራዮች እና ማህበረሰቦች ተሳትፈዋል። ተሳትፎ ከሰማይ-ጠቀስ ሕንጻዎች ተከራዮች ጋር በጋራ በነደፍናቸው እሴቶች እና መርሆዎች ይመራል።

2



## ተከራዮች ወደ ሌላ ቦታ ይዛወራሉ

በቦታው ያሉት ከቦታ ወደ ቦታ የሚያዛውሩ ቡድኖቻችን እንደ ፍላጎቶችዎ እና ምርጫዎችዎ ትክክለኛውን ቤት ለማግኘት ከተከራዮች እና ከማህበረሰብ አገልግሎቶች ጋር በቅርበት ይሰራሉ። እያንዳንዱ ተከራይ ሁለት ተስማሚ እድሎች ይሰጠዋል፣ በሚዛወሩበት እና በአዲሱ ቤታቸው በሚሰፍሩበት ጊዜም ቀጣይነት ያለው ድጋፍ ይሰጣቸዋል።


3



## እቅድ ማውጣት

ከአሁኑ ተከራዮች እና ማህበረሰቦች ጋር ጥልቅ ተሳትፎ ማድረግ የጋራ ራዕይ የአዳዲስ ቤቶችን እና የታደሰ ሰፈሮችን ዲዛይን እንደሚመራ ያረጋግጣል።

4



## በጥንቃቄ ማፍረስ

እያንዳንዱ ሕንፃ በጥንቃቄ ይፈርሳል። እንደ ህንፃው ሁኔታ ይህ ሂደት እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ሊወስድ ይችላል። ማህበረሰቡን በሂደቱ ወቅታዊ መረጃ እንዲያገኝ እናደርጋለን እና ቁሳቁሶች በተቻለ መጠን እንደገና ጥቅም ላይ እንዲውሉ እናደርጋለን።

5



## የግንባታ ቦታ ዝግጅት እና ግንባታ

እቅድ እና ዲዛይን ከፀደቀ በኋላ እና ገንቢ (ቤቱን የሚሰራ ድርጅት) ከተሾመ በኋላ አዳዲስ ቤቶችን ለመገንባት ግንባታው ይጀምራል። ይህ ከሁለት እስከ ሶስት አመታት ሊወስድ ይችላል። በዚህ ሁሉ ሕብረተሰቡ በሂደቱ ላይ የሚደረጉ ዝግጅቶች እንዲያውቅ እና እንዲሳተፍ ይጋበዛል።

6



## አዲስ እና ተመላሽ ተከራዮች እንኳን በደህና መጣችሁ!

አዲሱ ማህበራዊ መኖሪያ ቤት ሲጠናቀቅ፣ ወደ ተለዋጭ መኖሪያ ቤት የተዛወሩ ነዋሪዎች ቀጣይነት ባለው ብቃታቸው እና ፍላጎታቸው መሰረት የመመለስ መብት ይኖራቸዋል። ለአዲስ ተከራዮችም ቤቶች ይቀርቡላቸዋል።

አዲስ ነገር ካለ ለማወቅ ይመዝገቡ

www.homes.vic.gov.au/sign-up-project-updates

ሆምስ ቪክቶሪያን ይከተሉ

ፌስቡክ/Facebook፦ @homesvicgov

ኢንስታግራም/Instagram፦ @homesvic

ሊንክድኢን/Linkedin @homes-victoria

# ማህበረሰባችን፣ እሴቶቻችን


ማህበረሰቦቻችን፡ እሴቶቻችን ለተከራዮች ያለንን ቁርጠኝነት የሚወክሉ የእሴቶች ስብስብ ነው፣ በመላው ሜልበርን ባሉ የሰማይ-ጠቀስ ፎቅ ቤቶች መልሶ ግንባታ ሂደትም ከተከራዮች ጋር እንዴት እንደምንገናኝ እና እንዴት እንደምናሳትፍ መመሪያ ይሰጣል።

ከታህሳስ ወር ጀምሮ ለእነርሱ በጣም አስፈላጊ የሆነውን ነገር እና ምን ማየት እንደሚፈልጉ ለማወቅ ከ700 በላይ የሆኑ ተከራዮችን አማክረናል። ተከራዮች በእያንዳንዱ እሴት ላይ ግብረ መልስ ሰጥተውናል እና እንደ በመደበኛነት አዲስ ነገር ሲኖር ማሳወቅን፣ WhatsApp ቡድኖችን፣ የተከራይ የድምፅ ቡድኖችን፣ የማህበረሰብ አያያዥ ፕሮግራሞችን፣ ከሚዛወሩት ተከራዮች ድጋፍ እና የመልሶ ግንባታ ጊዜን ግልጽ ማድረግ።

አሁን ያገኘነው ግብረ መልስ እና እሴቶቹን እንዴት እንደቀረጸ የሚገልጽ ዘገባ በማጠናቀቅ ላይ እንገኛለን፣ እሱም በጁላይ ወር መጨረሻ የምናወጣው ይሆናል።

## የማህበረሰብ እሴቶች እና መርሆዎች ምንድናቸው?

በመጀመሪያው ያገኘነው ግብረ መልስ መሰረት፣ **ማህበረሰቦቻችን፡ እሴቶቻችን** የሚለውን ረቂቅ አዘጋጅተናል። የማህበረሰባችን እሴቶች እና መርሆች ለተከራዮች ያለን ቁርጠኝነት ይሆናል፣ ይሄም በሜልበርን ያሉትን ረጃጅም የቤት ሕንጻዎች እንደገና የምንገነባበት ወቅት ከእነሱ ጋር እንዴት እንደምንሠራ መመሪያ ይሆናል።






## በኪራይዎ የሚኖሩ ለውጦችን ለማቀድ ተጨማሪ ጊዜ ይኖርዎታል

አሁን በኪራይዎ ላይ ከሚኖሩ ለውጦች ጋር ነገሮች ለማቀናጀት እስከ ኖቬምበር 2024 ድረስ ጊዜ አለዎት።

የቤት ኪራይዎ ትክክለኛ መጠን እንድንተምን እንዲያግዘን እና እርስዎ መክፈል ያለብዎትን ብቻ እንዲከፍሉ ለማረጋገጥ፣ እባክዎ በቤተሰብዎ ገቢ ወይም ሁኔታ ላይ የተደረጉ ለውጦች ያሳውቁን።

ማንኛውም አይነት ጥያቄ ካለዎት ወይም እርዳታ ከፈለጉ፣ እባክዎን በ www.housing.vic.gov.au/contact-housingvic በኩል ያግኙን

ማንኛውም ተከራይ ከሚያገኘው ገቢ ከ25 በመቶ በላይ ለኪራይ እንዳይከፍል ቅናሽ ለማግኘት ማመልከት ይችላል።

በገበያው ሂሳብ ኪራይ ከሚከፍሉት ቤተሰቦች የሚገኘው እያንዳንዱ ዶላር የሕዝብ መኖሪያ ቤቶችን የተሻለ ለማድረግ ይውላል። ኪራዩ ህንፃዎቹን ለመጠገን እና ለተከራዮች አገልግሎቶች፣ ማለትም እንደ ጽዳት እና ሌሎች ወሳኝ የመኖሪያ ቤት አገልግሎቶች አቅርቦትን ለሁሉም የህዝብ መኖሪያ ቤቶች በሰማይ-ጠቀስ ቤቶች ጨምሮ ለመስጠት ይውላል።

**በሕዝብ መኖሪያ ቤት ውስጥ ያለ ተከራይ ከገቢው ከ25 በመቶ በላይ ለኪራይ መክፈል የለበትም። ይህ ጥበቃ ከሌለው የግል የኪራይ ገበያ በጣም የተለየ ነው።**



## የጥገና ትኩረት

**ሆምስ ቪክቶሪያ ተከራዮች እዚያ በሚኖሩበት ወቅት በሰማይ-ጠቀስ ሕንጻዎች ላይ ቀጣይ ጥገና ለማድረግ ቁርጠኛ ነው።**

እንደ አሳንሰር (ሊፍት)፣ የቧንቧ እና የኤሌትሪክ አገልግሎቶች ያሉ ነገሮች ስራቸውን መቀጠላቸውን እያረጋገጥን፣ በሰማይ-ጠቀስ ሕንጻዎች ቤቶች የበለጠ ምቹ እና ለኑሮ የሚስማሙ ለማድረግ ላቅ ያሉ ነገሮች እና ማሻሻያዎችን ማድረጋችን እንቀጥላለን።

ለተከራይ አስተያየት ምላሽ ለመስጠት፣ አስቸኳይ ላልሆኑ ጥገናዎች የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል፣ በሰሜን ሜልቦርን፣ ፍሌሚንግተን፣ ሰሜን ሪችመንድ፣ ካርልተን እና ኮሊንግዉድ በሰማይ-ጠቀስ ሕንጻዎች ቦታዎች ላይ የአካባቢ የጥገና ሰራተኞችን ስምሪት ተግባራዊ አድርገናል። ፕሮግራሙ በአገልግሎቱ 95 በመቶ የተከራይ እርካታ አስመዝግቧል፣ ለተከራዮችም ጥሩ ውጤቶችን እያስገኘ ነው።

በሺህዎች የሚቆጠሩ ተከራዮችም ለረጅም ጊዜ በቆየው በሰማይ-ጠቀስ ሕንጻዎች ማሻሻያ መርሃ ግብር ማድ ቤቶችን እና መታጠቢያ ቤቶችን በማሻሻሉ፣ ባለ ሁለት መስተዋት መስኮቶችን በመግጠሙ እና የህንፃ ፊት ለፊት እና የማህበረሰብ ክፍሎችን በማደሱ ተጠቃሚ ሆነዋል።

**ቤትዎ ጥገና ወይም እደሳ የሚያስፈልገው ከሆነ በሦስት መንገዶች የቤቶች ቢሮን ማግኘት ይችላሉ፡-**

**ይደውሉ** 13 11 72

**ኢሜይል** tenant.maintenance@dffh.vic.gov.au

**ኦንላይን** www.maintenance.forms.homes.vic.gov.au

# ከቦታ ወደ ቦታ የመዛወር ወቅታዊ መረጃ

## ፍሌሚንግተን እና ሰሜን ሜልበርን

በቅርብ ወራት፣ ከሰሜን ሜልበርን እና የፍሌሚንግተን በሰማይ-ጠቀስ ፎቆች የሚነሱ ተከራዮች በቪክቶሪያ ስትሪት፣ ፍሌሚንግተን ወደተገነባው አዲስ ማህበራዊ መኖሪያ ቤት እየገቡ ነው። ይህ ቀደም ሲል የቪክቶሪያ ስትሪት ፕሮጀክት አካል ሆነው ወደ ሌላ ቦታ የተዛወሩ ተመላሽ ተከራዮችን ያካትታል። እነዚህ ክፍሎች በአዲሶቹ ቤቶቻቸው ምቹ የመኖሪያ ቦታዎች እና የግል መገልገያዎች እየተዝናኑ ባሉ ተከራዮች በፍጥነት እየተወሰዱ ነው።

ተከራዮች በቅርቡ በአቦስፎርድ ስትሪት፣ ሰሜን ሜልቦርን በቅርብ የተገነቡ አዳዲስ ቤቶችን ያገኛሉ። ይሄ እርስዎ አዲስ ቤትዎ ለማድረግ እንዲያስቡበት ከቀረቡት በአካባቢው ካሉት ሁለት አዳዲስ ግንባታዎች ሁለተኛው ነው። በአቦትስፎርድ ስትሪት፣ ሰሜን ሜልበርን ያሉትን አዲሶቹን ቤቶች ግምት ውስጥ ማስገባት ከፈለጉ እባክዎን የመዛወር ሰራተኛውን ያሳውቁ። የግንባታ ቦታውን ለመጎብኘት እና በአካባቢዎ ያሉትን አዳዲስ ቤቶች ለማየት ፍላጎትዎን ለመግለጽ ጊዜው አሁን ነው።

በቅርቡ ወደ አዲስ ቤት የሚዛወሩ ከሆነ እና ስለ ሂደቱ ማንኛውም አይነት ጥያቄ ካለዎት እባክዎን የመዛወር ሰራተኛውን ያነጋግሩ። የማዛወር ሰራተኛው ማን እንደሆነ እርግጠኛ ካልሆኑ ወይም አድራሻው ከሌልዎት፣ እባክዎን በ **relocationsteam@homes.vic.gov.au** ኢሜል ይላኩ ወይም ለእርዳታ የአካባቢዎን የመኖሪያ ቤት ቢሮ ያነጋግሩ።

በሌሎች ሰማይ-ጠቀስ ሕንጻዎች ላይ ላሉ አባወራዎች እና አሁን መዛወር ለማያስፈልጋቸው፣ መረጃ እና ምክር ለመስጠት መሞከራችንን እንቀጥላለን፣ ስለዚህ የመዛወር ጊዜ ሲደርስ ሙሉ መረጃ እንደተቀበሉ እና ድጋፍ እንደተሰጠዎት ይሰማዎታል።

## ተጨማሪ መረጃ

**ይሄን ይጎብኙ፡-** homes.vic.gov.au/high-rise-victoria

**ኢሜይል፡-** enquiries@homes.vic.gov.au

**ወደ ሃውሲንግ የጥሪ ማዕከል በ** 13 11 72 **ይደውሉ**

## ሆምስ ቪክቶሪያን ይከተሉ

**ፌስቡክ/Facebook፡-** @homesvicgov

**ኢንስታግራም/Instagram፡-** @homesvic

**ሊንክድኢን/Linkedin** @homes-victoria

## ትርጉሞች

homes victoria

VICTORIA State Government

በቪክቶሪያ መንግስት የተፈቀደ እና የታተመ፣ 1 Treasury Place, Melbourne. © State of Victoria, ሆምስ ቪክቶሪያ (የቤቶች ዳይሬክተር)፣ ጁላይ 2024። በፊንስበሪ ግሪን፣ ሜልበርን ቪክቶሪያ የታተመ (HV010324)